ዶክተር ሄንሪ ኪሲንጀር በበርካታ አጋጣሚዎች «አዲስ የዓለም ሥርዓት» ምሥረታ ግባቸው እንደሆነ ተናግረዋል:: የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ጋዜጠኛው ፖል ስኮት፣ «ረዳቶቻቸው እንደሚሉት ከሆነ፣ ኪሲንጀር የምግብ አቅርቦትን በመቆጣጠር ሕዝብን መቆጣጠር እንደሚቻልና ኃይልን፣ በተለይም ነዳጅ ዘይትን፣ በመቆጣጠር ሀገራትንና የፋይናንስ ሥርዓታቸውን መቆጣጠር እንደሚቻል ያምናሉ:: ኪሲንጀር የዓለም የገንዘብ ሥርዓትን ጨምሮ የምግብና ነዳጅ ዘይት አቅርቦትን በዓለም አቀፋዊ ቁጥጥር ሥር በማድረግ በተባበሩት መንግሥታት መዋቅር ሥር የሚንቀሳቀስ ብዙም ጠበቅ ያላለ የዓለም መንግሥት ከ1980 ዓ.ም. በፊት እውን ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አላቸው» ሲል ጽፏል::

እርግጥ ነው፣ ኪሲንጀር የጌራልድ ፎርድ የፕሬዚዳትነት ዘመን ሲያበቃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ለቅቀዋል:: ይሁን እንጂ፣ ፕሬዚዳንት ካርተር በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት የሾሟቸው ሳይረስ ቫንስና ኤድመንድ ማስኪ የውጭ ግንኙነት ካውንስል አባላት ነበሩ:: የሮናልድ ሬገንና ጆርጅ ቡሽ ተሿሚዎችም እንዲሁ በአብዛኛው የካውንስሉ አባላት ነበሩ:: በዚህም መሠረት፣ የውስጠ-ዐወቆቹ እቅድ ያለምንም ዕንቅፋት ቀጥሏል:: በእርግጥ፣ የውጭ ግንኙነት ካውንስሉ ከሁለቱ ትላልቅ ፓርቲዎች፣ ማለትም ሪፐብሊካንና ዴሞክራት፣ ጋር የተሳሰረ አይደለም:: ይሁንና፣ በሁለቱም ውስጥ ሰርጎ በመግባት ይንቀሳቀሳል::

የውጭ ግንኙነት ካውንስል ተጽዕኖ በመንግሥት ሥልጣን ብቻ ሳይወሰን በመገናኛ ብዙኃንም ጭምር ይንጸባረቃል:: ቀጣዮቹ የመገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች ሁሉ ዳይሬክተሮች፣ አዘጋጆችና ጸሐፊዎች የመሰሉ የካውንስሉ ቁልፍ አባላት አሏቸው:: ናሽናል ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኤን.ቢ.ሲ.) ኮሎምቢያ ብሮድካስቲንግ ሲስተም (ሲ.ቢ.ኤስ.)፣ *ታይም፣ ላይፍ፣ ፎርቹን፣ ሉክ፣ ኒው ዮርክ ታይምስ፣ ዋሽንግተን ፖስት፣ ሎስ አንጀለስ ታይምስ፣ ኒው ዮርክ ፖስት፣ ዴንቨር ፖስት፣ ሳተርዴይ ሪቪው፣ ቢዝነስ፣* ማክሚላን ኩባንያ ወዘተ... እያለ ዝርዝሩ ይቀጥላል::



Scanned with CamScanner

የውጭ ግንኙነት ካውንስሉ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ዋነኛ መገናኛ ብዙኃን የሚከተሉትን አቅጣጫ በመምራት የዓለም አቀፋዊነት፣ የእርስ በርስ መደጋገፍና የአንድ ዓለም መንግሥት አስተምህሮዎች፣ በሕዝቡ ዘንድ ሰርጸው ከመግባት ባለፈ አስተሳሰቡን እየለወጡት መሆኑ ብዙም ሊያስገርመን አይገባም:: ከዚህ በተጨማሪም፣ መገናኛ ብዙኃኑ ዶክተር ኪሲንጀር በ1980 ዓ.ም. እውን ይሆናል ባሉት በተባበሩት መንግሥታት መዋቅር ሥር የሚንቀሳቀስ ብዙም ጠበቅ ያላለ የዓለም መንግሥት ምሥረታ እቅድ በበርካታ ሀገራት ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ አድርገዋል:: የዶክተር ኪሲንጀር ሕልም በተባለው ዓመት እውን ባይሆንም፣ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽና ሌሎች መሪዎች በ1990ዎቹ ዓመታት የአዲስ ዓለም ሥርዓት ምሥረታን እያወጁ ቆይተዋል::



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ 7

# የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች

**«የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል»**

(የማቴዎስ ወንጌል 10:30)

በመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች ልዩ ትርጉም አላቸው፡፡ እግዚአብሔርም እነኝህን ቁጥሮች ሙሉእ በሆነ፣ ወለም ዘለም በማይልና በማያቋርጥ መልኩ ይጠቀምባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ፍጹም የሆነውን ፍጹም መሆኑን፣ እንዲሁም ሰይጣናዊ የሆነውን ሰይጣናዊ መሆኑን ለመግለጽ ቁጥሮችን ይጠቀማል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሰፈሩት ቁጥሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያላቸው ትርጉም ይህን ይመስላል፡፡

1. አንድነት
2. መለያየት ወይም ምስክር
3. እግዚአብሔር፣ መለኮታዊ ፍጹምነት ወይም እግዚአብሔርነት
4. ዓለም ወይም የፈጠራ ሥራ
5. ጸጋ
6. ሰው (ኃጢአተኛ)
7. ፍጹምነት
8. ትንሣኤ (የኢየሱስ ክርስቶስ የግል ቁጥር)
9. ፍጻሜ
10. መደበኛ ፍጹምነት
11. ሥርዓት የለሽነት
12. መንግሥት
13. ኃጢአት፣ ዓመፅ እና ሰይጣን
37. የእግዚአብሔር ሕያው ቃል
40. ግብረ-ገባዊ ፈተና



Scanned with CamScanner

መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈባቸው የዕብራይስጥና ጽርእ ቋንቋዎች እያንዳንዱ ፊደል ልክ እንደ ሮማውያን ፊደላት የሚወክል ነው:: እንደሚታወቀው፣ በሮማውያን ዘንድ V 5፣ L 50፣ C 100፣ M 1000 ይወክላሉ::

ለምሳሌ ያህል፣ 888 የኢየሱስ (ትንሣኤ) ቁጥር ነው:: የሚለውን ቃል በግሪክኛ ፊደላት ስንጽፈው ይህንኑ አኃዝ ይሰጠ

I 10

E 8

S 200

O 70

U 400

S 200

888 ድምር

ይህ ቁጥር ሦስት ስምንቶችን ያቀፈ ነው:: በሌላ በኩል፣ በ37 ቁጥር የሚገለጸው «የእግዚአብሔር ቃል» ጭምር ነው:: በእግዚአብሔርነቱ ደግሞ በ3 ቁጥር ይገለጻል:: ስለዚህም፣ ሦስት ቁጥሮች ማለትም 8፣ 37 እና 3 በሙሉ ክርስቶስን የሚ ናቸው:: 8x37x3 ደግሞ 888 ይሰጠናል:: ይህም ቁጥር ከስሙ ጋር አንድ ዓይነት ነው:: ድምሩ የ8 ቁጥር ብዜት (111x8) መሆ መዘንጋት የለብንም::

«ኢየሱስ» ለሚለው ቃል የግሪክኛ ፊደላት 888 ቁጥርን የ አጋጣሚ ሆኖ ነው? አይደለም:: እግዚአብሔር በመጽሐፍ ውስጥ በሙሉ የኢየሱስ መጠሪያዎች ከ8 ቁጥር ጋር እንዲ አድርጓቸዋል:: ቀጣዮቹን የኢየሱስን መጠሪያዎች ከግሪክኛ ፊ ጋር በተያያዘ ያላቸውን ዋጋ እንመልከት::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ክርስቶስ | - 1480 | = | (185x8) |
| መድኃኔዓለም | - 1408 | = | (176x8) |
| ጌታ | - 800 | = | (100x8) |

እርሾ የኃጢአት ምልክት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም 13 ጊዜ ተጠቅሷል:: የዚህ ቃል እንግሊዝኛው አኃዛዊ ዋጋ 455 (35x13) ነው:: ለምሳሌ ያህል፣ እርሾ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13:33 ላይ ተጠቅሷል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ «ግብዝ» የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ 13 ጊዜ ተጠቅሷል:: የሰይጣን መጠሪያ የሆነው «ደራጎን» እንዲሁ 13 ጊዜ ተጠቅሷል::

ቀጣዮቹን የሰይጣን ማዕረጎች ዋጋ እንመልከት::

ደራጎን - 95 = (75x13)

ብሊያል - 78 = (6x13)

ተፈታታኝ - 1053 = (81x13)

ነፍሰ-ገዳይ - 1820 = (140x13)

እባብ - 780 = (60x13)

በዮሐንስ ራእይ 20:2 የሰፈረው «ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን» የሚለው የእንግሊዝኛው ሐረግ አኃዛዊ ዋጋ 2197 (13x13x13) ነው:: ታዲያ፣ 13 የሰይጣን ቁጥር ለመሆኑ ያጠራጥራል? 13 እንደ ገደ-ቢስ ቁጥር ተደርጎ የሚወሰደውስ በዚሁ ምክንያት ይሆን?

አሁን ደግሞ 6 ቁጥርን እንመልከት:: ሰው የተፈጠረው በስድስተኛው ቀን ነው:: ሰው ኃጢአት ውስጥ በሚወድቅበት ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 «ሰው» የሚለው ቃል 6 ጊዜ ተጠቅሷል:: በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 6 ስለ ሰው ክፋት ተጽፏል:: በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 13 ላይ ደግሞ የሰው ክፋት መጨረሻው ተጽፏል:: በወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2 ምዕራፍ 2 ላይ ስለ «የጥፋት ልጅ» የወደፊት ዕጣ ተጽፏል:: በዚሁ ምዕራፍ ላይ «የጥፋት ልጅ»፣ «የዓመፅ ሰው»፣ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ»፣ «ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው»፣ «ዓመፀኛ»፣ «የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች፣ በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን ነው» ሲል 6 ጊዜ ይጠቅሰዋል::

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 6 ላይ ስለ የጥፋት ሰው (ፀረ-ክርስቶስ) መነሣት ተጽፏል:: በዮሐንስ ራእይ 18 (6x6x6) የአጋንንት ማደሪያ



Scanned with CamScanner

በእርግጠኝነት መናገር የምንችለው ሌላኛው ነጥብ የመጪው ፀረ-ክርስቶስ መጠሪያ ስም አኃዛዊ ዋጋ 666 እንደሚሆን ነው:: ይኸውም ፀረ-ክርስቶስ አሁን ባለንበት ዘመን ይመጣ ይሆን? በአሁኑ ወቅት ከመጋረጃው በስተጀርባ እየተንቀሳቀሰ ከሆነ፣ በአሁኑ ዘመን ብቅ የማይልበት ምንም ምክንያት የለም:: ምናልባት ከሮትሺልድ ቤተሰብ መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል::

ስለ ሄንሪ ኪሲንጀር ምን ማለት እንችላለን? በ1976 ዓ.ም. ከአይሁዳዊነት ቢወገዙም፣ በትውልዳቸው የአይሁድ እምነት ተከታይ ናቸው፤ በሌላ በኩል፤ የምሥጢራዊ ማኅበራት ውስጠ-ዐወቅና «የሰላም ሰው» ናቸው:: ኪሲንጀርን ከ666 ጋር ያያያዛቸው ሰውም አለ::

ኪሲንጀር በእንግሊዝኛ ሲጻፍ የፊደላቱ ዋጋ ተደምረው 666 ይሰጡናል:: የ«ሄንሪ» ፊደላት ድምር ደግሞ 420 (6x70) ነው:: የመካከለኛ ስማቸው የመጀመሪያው ፊደል «ኤ» አኃዛዊ ዋጋ 6 ነው:: ይሁን እንጂ፣ ይህ ሁሉ ስሌት ኪሲንጀር ፀረ-ክርስቶስ ለመሆናቸው ማረጋገጫ አይደለም::

ኪሲንጀር ለዓለም አገዛዝ ሊቀርቡ የሚችሉ ማለፊያ እጩ ቢሆኑም፣ ችግሩ በሕዝብ ዘንድ መታወቃቸው ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:: 2:7-8 ላይ የጥፋት ሰው የሚገለጠው መንፈስ ቅዱስ ከመንገዱ ሲወገድ ብቻ እንደሆነ ተጽፏል:: ያም ሆኖ፣ ኪሲንጀር መንገዱን ለሰው 666 እየጠረጉለት ነው::

በዚህ መጽሐፍ ላይ የክፋት ምሥጢር «ምሥጢረ 666» በሚል ተገልጿል:: ይህም የሆነበት ምክንያት የሰይጣን ሴራ ማክተሚያው ላይ የሚደርሰው በሰው 666 አማካኝነት በመሆኑ ነው:: ይኸው እኩይ ሴራ 13፣ 6 እና 666 ቁጥሮችና ብዜታቸው ላዩ ላይ የሰፈሩበት ይሆናል::

ኢሉሚናቲን ብንመለከት በተለያየ መልኩ ከነኝህ ቁጥሮች ጋር የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን:: የአዳም ዌይስሆፕት ስም በእንግሊዝኛ ሲጻፍ 13 ፊደላትን የያዘ ነው:: «ሰው» ማለት ትርጉም ያለው «አዳም» የተወለደው የካቲት 6 (1748 ዓ.ም.) ነው፤ የሰው ቁጥር ደግሞ 6 ነው:: ኢሉሚናቲ የተቋቋመው በ1776 ዓ.ም. (296x6) ነው:: ኢሉሚናቲ ኮሙኒስት ሜኒፌስቶን መጀመሪያ ጊዜ ለንባብ ያበቃው



Scanned with CamScanner

በ1848 ዓ.ም. (308x6) ነው። ካርል ማርክስ የተወለደው በ1818 ዓ.ም (303x6) ነው። ዌይስሆፕት የሞተው በ1830 ዓ.ም. (305x6) ነው።

ኢሉሚናቲ ከተመሠረተበት (1776 ዓ.ም) ኮሙኒስት ማኒፌስቶ ለኅትመት እስከበቃበት (1848 ዓ.ም) ድረስ 72 ዓመታት (12x6) አልፈዋል። የኢሉሚናቲ ምልክት የታተሙበት የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፌደራል ሪዘርቭ አዋጅ የወጣው በ1913 ዓ.ም. ነው።

ያም ሆኖ፣ ሕይወታችን በቁጥሮች የሚገዛ ባለመሆኑ ስማችን 13 ፊደላት ቢኖሩትም እንኳን ከዚህ አጉል እምነት ተነሥተን መፍራት የለብንም። ይሁን እንጂ፣ ፀረ-ክርስቶስን በሚመለከት የቁጥሮችን፣ በተለይም የ666፣ ትርጉም በሥራ ላይ መመልከታችን አይቀርም። ከጥቂት ዓመታት በፊት የወጣ አንድ ሪፖርት እንደሚያረጋግጠው፣ በብራሰልስ የሚገኘው አዲስ የገንዘብ ሥርዓት (ዩሮ) ለመዘርጋት የቆመው የኮምፒዩተር መረብ መነሻ የኮድ ቁጥሩ 666 ነው።



Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ 8

# ኃይል 13

**«ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላ በክፉው እንደተያዘ እናውቃለን።»**

(የዮሐንስ መልእክት 1:: 5:19)

በዚህች ዓለማችን ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ያለ አንድ ሰይጣናዊ ኃይል አለ። ይኸው ኃይል በሚችለው መንገድ ሁሉ ማንተሙን በማኅበረሰቡ ላይ እያሳረፈ ነው። ኃይሉ ከእግዚአብሔርና ከሰው ልጅ ፍላጎት አንጻር እየሠራ ያለ የሴራዎች ሁሉ ማእከል ነው። ለዓላማው ማስፈጸሚያነት የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ፈቃደኛ ያልሆኑትንም ጨምሮ አግባብቶ ይጠቀምባቸዋል። ሥራውን የማይጠራጠሩትን ወገኖች ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሲጠቀምባቸው፣ በጎ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች አእምሮ ይመርዛል። ድኻውንም ሆነ ሀብታሙን በመመልመል ለሁለቱም ወገኖች፣ እንዲያውም ፈቃዱን ለሚፈጽሙ ሁሉ ጥቅም እንደሚያስገኝላቸው ቃል ይገባላቸዋል። ለድኻው ሀብት፣ ለሀብታሙ ሥልጣን ይሰጣቸዋል። የማደግ ጉጉት ላላቸው ደግሞ ዝናንና ሥልጣንን ያስጨብጣቸዋል።

ይህን ኃይል የሚቋቋሙ ሰዎች መራር ጥቃት የሚያጋጥማቸው ሲሆን፣ ሊያጋልጠው የሚሞክርም ውርደትንና የስም መጥፋትን በራሳቸው ላይ ይጋብዛሉ። ይሁንና፣ ይህን የእግዚአብሔርንና የሰው ልጅን ጠላት ካላጋለጥን፣ ከፈጣሪ ሳይሆን ከዚሁ እኩይ ኃይል ጐን እንሰለፋለን። ከኢሉሚናቲ፣ ራውንድ ቴብል፣ የውጭ ግንኙነት ካውንስል፣ ቢልደርበርገሮችና የዓለም መንግሥትን ለመመሥረት ከሚሯሯጡት ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ተቋማት በስተጀርባ ያለው ይኸው ኃይል ነው።

ኃይል 13 የአጋንንት አለቃ የሆነው ሰይጣን ራሱ ነው። ሰይጣን የጨለማው ዘመን ምናባዊ ፍጡር ሳይሆን በዓይን የማይታይ ኃይለኛ ፍጡር ነው። ኃይል 13 የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርም



Scanned with CamScanner

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም «ባቢሎን» የሰይጣንን የውሸት ግዛተ-መንግሥት የሚወክል ነው::

በትንቢተ ኢሳይያስ የሰፈረው ይህ ምንባብ ከምድራዊው ንጉሥ መኩራራት የበለጠ የሚያሳየን ነገር አለው:: የሰይጣንን የመጀመሪያ ሁኔታና ውድቀት በመጠኑም ቢሆን የሚገልጽ ነው:: ሉሲፈር እንደ ፍላጎቱ ተቀባይነትን ሲያጣ የፈጣሪውን ሥልጣን በመጨበጥ መመለክን ተመኘ:: እንዴት እንደሆነ ባይነገረንም፣ ሰይጣን በርካታ መላእክት በእግዚአብሔር ላይ እንዲያምፁ በመምራት ታማኝነታቸውንና አምልኳቸውን አግኝቷል::

በማቴዎስ ወንጌል 25:41 ላይ፣ «እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ» ይላል:: ሰይጣን የዚህ እኩይ መንፈሳዊ ዓለም መሪ መሆኑ ግልጽ ነው:: በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ አጋንንት በጣም ብዙ እንደሆኑ ተገልጿል:: አጋንንቱ የሚንቀሳቀሱት በሰማየ-ሰማያትና በመንፈሳዊው ዓለም ቢሆንም፣ በምንኖርባት ዓለም ላይ ከፍተኛ ተሰሚነት አላቸው:: «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ:: መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ::» (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:11-12)

ይሁን እንጂ፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የወደቁ መላእክት ታማኝነት አልበቃ ብሎት፣ ሰይጣን የሰው ልጅን እንደተፈጠረ ሊያጠቃው ተሰልፏል:: ጥቃቱን የሰነዘረው ሔዋንን «እንደ እግዚአብሔር ትሆኛለሽ» በማለት የተከለከለውን ፍሬ እንድትበላ በመገፋፋት ነው:: አዳምና ሔዋንን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲያከብሩ በማድረግ ኃጢአት ውስጥ ከትቷቸውና የዋህነታቸውን ገፍፏቸው ሲያበቃ የነሱንና የተወላጆቻቸውን ሁሉ ታማኝነት ይገባኛል አላቸው::

የአዳምና ሔዋን ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ እንደማንኛውም አነስተኛ ስሕተት የሚቆጠር አይደለም:: በጣም አሰቃቂ፣ ጐጂና አጥፊ ከመሆኑ የተነሣ እነኝህ ሁለት የሰው ልጅ የመጀመሪያ ወላጆች



Scanned with CamScanner

እግዚአብሔር ሰይጣንን ማምለኩ የማይታሰብ ቢሆንም፣ ዲያቢሎስ መሞከሩ አይከፋም የሚል አቋም የያዘ ይመስላል። ምናልበት ሥጋ ለብሶ ወደዚህች ምድር የመጣው እግዚአብሔር እንደ የሰው ልጅ ደካማ መስሎት ይሆናል። ክርስቶስ ለዚሁ ድፍረቱ የሰጠው ምላሽ «ሂድ፣ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ብቻ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና» የሚል ነው። (የማቴዎስ ወንጌል 4:4)

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች ለመፍጀት ባደረገው ሙከራ እንዳልተሳካለት ሁሉ፣ ኢየሱስን ለመገፋፋት ያደረገው ጥረትም ከሽፎበታል። ያም ሆኖ፣ በታሪክ እንደታየው ሰዎችንና ሀገራትን በመቆጣጠሩ ረገድ በተደጋጋሚ ተሳክቶለታል፤ ስኬታማነቱ በዘመናችን ባለው ዓለም አቀፋዊ ሴራ ጭምር ቁልጭ ብሎ ይታያል።

## ኃይል 13 በሥራ ላይ

ሰይጣን ለ6000 ዓመታት ያህል በሰው ዘር ላይ እየሠራ ነው። ዓላማውም መቼም ቢሆን ተለውጦ የማያውቀው የሰው ልጅ አምልኮን ማግኘት ነው። ለዓላማው ማስፈጸሚያነት የሚጠቀምባቸው እቅዶችና ዘዴዎች ከዘመን ዘመን የተለያዩ ናቸው። እንቅስቃሴው፣ በሰው ዘር ላይ የዘረጋውን የቁጥጥር መረብ ለማጠናከር የሚገለገልባቸው እስትራቴጂዎች፣ እንዲሁም ሰይጣናዊ አምልኮን ለማስፈን የሚያደርገው ድርጊት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተለዋዋጭ ናቸው።

ከቀደምት ሥልጣኔዎች መካከል አንዱ የግብፅ ነው። ስለዚሁ ሥልጣኔ የምናውቀውን ነገር በአብዛኛው ያገኘነው የቼኦፕስ ፒራሚድ በሚል መጠሪያ ከሚታወቀው ታላቁ ፒራሚድ ነው። ኃይል 13 በዚህ አጋጣሚ የሰው ልጅን በባርነት ለመግዛት የሞከረው ሥነ-ፈለክን (*አስትሮኖሚ*) እና ሃይማኖትን በመጠቀም ነው።

«በምድራችን ከተገነቡት ትላልቅ ሕንጻዎች መካከል ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው» ይህ ፒራሚድ መቼ እንደተገነባ በትክክል አይታወቅም፤ ይሁንና፣ በርካቶች በ2700 ዓ.ዓ. (450x6) አካባቢ መገንባቱን ይስማማሉ። ይህም የጥፋት ውኃ ከመምጣቱ ከ350 ዓመታት በፊት መሆኑ ነው። ታላቁ ፒራሚድ የሰይጣን ምልክቶች የሰፈሩበት ሕንጻ ነው። ፒራሚዱ የሚሸፍነው መሬት ስፋት 13



Scanned with CamScanner

በሚያዛባው ምሥጢራዊ ተጽዕኖ ግራ ተጋብተዋል:: ይህ ሁኔታ የታወቁ የሳይንስና ኤሌክትሮኒክስ ሕግጋትን የሚጻረር ነው:: ስውርነት፣ የፈርኦን እርግማን፣ አስማት፣ ጥንቆላ፣ ወዘተ... እያልን ብንጠራውም፣ ፒራሚዱ ማብራሪያ ካልተገኘለት ምሥጢር ጋር የተያያዘ ነው:: ፒራሚዱን በሚመለከት የሳይንስ ሕግጋትን የሚጥስ አንድ ኃይል አለ::.

ናፖሊዮንን ጨምሮ በርካታ ነገሥታትና መሪዎች ታላቁን ፒራሚድ እየጐበኙ እያለ ከሰብአዊ ባሕርይ ውጭ የሆኑ ገጠመኞች እንዳጋጠሟቸውና ሕይወታቸው እንደተገለጸላቸው ተናግረዋል:: ታዲያ፣ ይህን ሁሉ የሚያደርገው ኃይል 13 እንጂ ሌላ ማን ይሆናል? ፒራሚዱ ራሱ የጥንት ግብፃውያን ስውር ጥበቦች መገለጫ ነው::

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አዳም ዌይስሆፕት የማኒኬይዝም አስተምህሮን የቀሰመው የዚህን ሃይማኖት ምሥጢር በግብፅ ቆይታው ካወቀው ኮልመር ነው:: ዌይስሆፕትም የኋላ ኋላ ኢሉሚናቲ የተሰኘውን ምሥጢራዊ ማኅበር መሥርቷል:: እንግዲህ፣ በጥንታዊት ግብፅ ስውር ጥበብ፣ በ1776 ዓ.ም. በተመሠረተው ኢሉሚናቲና በ1913 ዓ.ም. በተቋቋመው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፌደራል ሪዘርቭ ሥርዓት መካከል ያለውን ትስስር መመልከት እንችላለን:: በ$1 ኖት ላይ ያለው ምልክት በአጋጣሚ የተገኘ እንዳልሆነ በላዩ ላይ ያሉት ዓይን፣ ጉነ-ሦስት፣ ፒራሚድ፣ የ1776 ዓመትና «አዲስ የዓለም ሥርዓት» የሚል ትርጉም የሚሰጠን NOVUS ORDO SECLORUM የሚለው መሪ ቃል በቂ አስረጅ ናቸው::

የኃይል 13 እቅድ በመሠረቱ የሰው ልጅን በማታለል አምልኮተ-ሰይጣን በሰፈነባት ምድር ሰዎችን በባርነት መግዛት ነው:: የጥፋት ውኃ ከመከሰቱ በፊት ባሉት ጥቂት ዐሥርተ- ዓመታት ኃይል 13 የዓለማችንን ሁኔታ ክፉኛ በማወክ ዓላማውን ለማሳካት ተቃርቦ ነበር:: የጥፋት ውኃ ሲከሰት በመላው ዓለም እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች ስምንት ብቻ ነበሩ::

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 6 በጊዜው ስለነበረው የሕዝብ ብዛት መጨመር፣ እንዲሁም የወንጀልና ንቅዘት መብዛት ተጽፏል:: በዚህ



Scanned with CamScanner

ሴሚራሚስ የመሠረተችው ሃይማኖት «አምልኮተ-ሰይጣን» በሚል መጠሪያ የሚታወቀው «ባቢሎናዊነት» የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው:: «የሰማይ ንግሥት» እና እንደ አምላክ የሚመለከው ልጇን ያቀፈው የሰይጣን ኑፋቄ የተለያዩ መጠሪያዎች እየወጡለት በመላው ዓለም ዙሪያ ተሰራጨ:: በከነዓን አስቶሮትና ባአል፣ በግብፅ ኢሲስና ሆረስ፣ በግሪክ አፍሮዳይትና ኤሮስ፣ እንዲሁም በጣልያን ቬነስና ኩፒድ የሚሉትን ስያሜዎች አግኝተዋል::

የባቢሎን ግንብ የተሠራው በጡብ ሲሆን፣ የተገነባውም በታሪክ ስሟ በገነነው ባቢሎን ውስጥ ነው:: ግንቡ 1140 ጫማ (190x6) ከፍታ ላይ ደርሶ ነበር:: ገንቢዎቹ መንግሥተ-ሰማያት እንደርሳለን ብለው ማሰባቸው በራሱ አስገራሚ ሲሆን፣ ግምቡም የሰይጣንን መንፈስ የሚያሳይ ነው:: ሰይጣን ሔዋንን ሲገፋፋት፣ «እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ» (ኦሪት ዘፍጥረት 3:15) ያለውን እዚህ ላይ ማስታወሱ ተገቢ ነው::

የአሦር ግዛት በባቢሎን እስከተደመሰሰበት ጊዜ ድረስ ለ666 ዓመታት ቆይቷል:: የባቢሎን ግንብ በአጭሩ ቀርቷል:: አንድ ቋንቋ የሚናገርና አንድ ሃይማኖት የሚከተል ሕዝብ የሚያቅፈው የአንድ ዓለም መንግሥት ምሥረታ መና ቀርቷል:: ይሁን እንጂ፣ ኃይል 13 ያሰበውን እስካላሳካ ድረስ «በቃኝ» ብሎ እጆቹን አጣጥፎ የሚቀመጥ አይደለም::

ከአሦር ውድቀት በኋላ ሰይጣን ትኩረቱን ያደረገው ናቡከደነፆርን የመሰለ ታላቅ ንጉሥ ባፈራችው ባቢሎን ላይ ነበር:: በናቡከደነፆር አገዛዝ ሥር ባቢሎን ትልቅ ውብ ከተማ ሆናለች:: ከተማዋ የተቆረቆረችው 150 ካሬ ማይል (25x6) ስፋት ባለው መሬት ላይ እንደሆነ ይገመታል:: ዙሪያዋን የከበባት ግንብ ከፍታው 100 ጫማ ሲሆን፣ ውፍረቱም 30 ጫማ (5x6) ነው:: ባቢሎን የተገነባችው ባቤል የተባለች ከተማ በነበረችበት ስፍራ ነው፤ የሁለቱም ከተሞች መጠሪያ ስም «ግርግር» የሚል ትርጉም ያዘለ ነው::

የባቢሎን ነገሥታት የአንድ ዓለም ሥርዓትና ሰይጣን የሚመለክበትን ሃይማኖት የመመሥረት ዓላማ ነበራቸው:: ግዛቱ



Scanned with CamScanner

የባቢሎን ውድቀት ደግሞ በትንቢተ ኢሳይያስ 13፡19-22 ላይ ተቀምጧል:: «እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ባፈረሰ ጊዜ እንደ ነበረው፣ የመንግሥት ክብር የከለዳውያንም ትዕቢት ጊዜ ባቢሎን እንዲሁ ትሆናለች:: ለዘላለም የሚቀመጥባት አታገኝም፣ ከትውልድም እስከ ትውልድ ድረስ ሰው አይኖርባትም፤ ዓረባውያንም ድንኳንን በዛ አይተክሉም፣ እረኞችም መንጎቻቸውን በዚያ አያሳርፉም:: በዚያም የምድረ በዳ አራዊት ያርፋሉ:: ጉጉቶችም በቤቶቻቸው ይሞላሉ፣ ሰጎኖችም በዚያ ይኖራሉ፣ በዚያም አጋንንት ይዘፍናሉ:: ተኩላዎችም በግንቦቻቸው፣ ቀበሮዎችም በሚያማምሩ አዳራሾቻቸው ይጮኻሉ፤ ጊዜዋ ለመምጣት ቀርቦአል ቀንዋም አይዘገይም::» ይህ ትንቢት በከፊል በፋርሱ ንጉሥ ዳሪየስ ተፈጽሟል:: የባቢሎንና ኢራቅ የመጨረሻው ፍጻሜ ደግሞ ጊዜውን ጠብቆ የሚመጣ ይሆናል::

በመጽሐፈ አስቴር በተጠቀሰው የንጉሥ አርጤክስስ ዘመነ-አገዛዝ ኃይል 13 የአይሁዳያንን ዘር ብሎም የእግዚአብሔርን ዕውቀት ለማጥፋት በድጋሚ ሞክሯል:: በጊዜው የሰይጣን መሣሪያ ሆኖ ያገለገለው በመጽሐፍ ቅዱስ «የኃጢአት ሰው» እንደሆነ የተገለጸለት የአማሌክ ተወላጅ የሆነው ሃማን ነው::

አይሁዳውያንን በሙሉ የማጥፋት የሃማን እቅድ ዳንኤልን ለማጥፋት የሞከሩት የባቢሎን ሹማምንት እንደዘረጉት ወጥመድ ተጨናግፏል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ሃማን ልክ እንደ የኢሉሚናቲው ሮበስፒር ራሱ ባቆመው የሰው መስቀያ ዕንጨት ላይ ለስቅላት ተዳርጓል::

ኮሙኒዝምን ለማስፈን ከተደረጉት ታላላቅ ሙከራዎች መካከል በ1300 ዓ.ዓ. አካባቢ በክሬት ደሴት የተሞከረው አንዱ ነው:: የኋላ ኋላ የግሪክ ከተማ መንግሥቷ ስፓርታ ገዢ ሊሳርገስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ7ኛው ክፍለ-ዘመን ይህንኑ የክሬት ሞዴል በግዛቱ ውስጥ ሥራ ላይ ለማዋል ሞክሯል::

ይህንንም ተከትሎ የእኩልነትና የጋራ ሕይወት መርሖዎች ስፓርታ ውስጥ ተግባራዊ ሆኑ:: የከተማ መንግሥቷ ዜጎች በጋራ የሚመገቡባቸውና የሚተኙባቸው ሕንጻዎች መኖር ጀመሩ:: አዲስ

ዘመን ሰይጣን የተማረውን ወገን አእምሮ ለመቆጣጠር የተጠቀመበት መሣሪያ ፍልስፍና ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ተራው ሕዝብ እውነተኛ ፈጣሪውን እንዳያውቅ ሐተታ መናፍስትን በስፋት ተጠቅሟል::

ከግሪክ ቀጥለው ዓለምን የተቆጣጠሩት ጨካኞቹና ኃይለኞቹ ሮማውያን ናቸው:: ኃይል 13 በዚህን ጊዜ ዓላማውን ለማስፈጸም የሞከረው ነገሥታት የሚመለኩበትን ሥርዓት በመዘርጋት ነው:: ሰይጣን የመሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጫ ሲቃረብ ቄሳርን እንደ አምላክ የሚመለክበትን ሁኔታ አመቻቸ:: ጁሊየስ ቄሳር (በእንግሊዝኛ ፊደላት ሲጻፍ 6+6) ከጥንታዊው የባቢሎን ምሥጢራት ያገኘውን ፓንቲፌክስ ማክሲመስ የተሰኘውን ማዕረግ ለራሱ በመስጠት ንጉሠ-ነገሥት ወአምላክ ሆነ::

ኢየሩሳሌምን ይዘው ከተማዋን ለ666 ዓመታት የገዙት ሮማውያን ናቸው:: የመጀመሪያዋን ቤተ-ክርስቲያን ለማጥፋት የሞከሩት የሮም ቄሳሮች፣ በተለይም ኔሮ፣ ናቸው:: በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌምንና ቤተ-መቅደሷን ያጠፋው ቄሳር ቲተስ ነው:: ከሰይጣን ተልእኮዎች መካከል አንዱ ኃይሌን ወይም ሥልጣኔን ይቀናቀኑኛል ብሎ የገመታቸውን አካላት ማጥፋት ነው::

የዘመናችንን ታሪክ ስንቃኝ ሰይጣን የሰው ልጅን ለማጥፋት ካልሆነም በባርነት ለመግዛት፣ እንዲሁም አምልኮ ለማግኘት የሚያደርገውን ቀጣይ ጥረት እናገኛለን:: የ6 እና 13 ቁጥር ማኅተሞቹም በአብዛኛው ዓላማውን ለማስፈጸም በሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ላይ ይታያሉ፤ በስማቸው ላይ ባይሆንም እንኳን በሌላ መንገድ እነኝህ ቁጥሮች ይንጸባረቁቸዋል:: ከ20ኛው ክፍለ-ዘመን እጅግ ጨካኝ ሰዎች መካከል አንዱ በርካታ የቅርብ ጓዶቹን ጨምሮ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ የፈጀው ጆሴፍ ቪሳርዮኖቪች ስታሊን (በእንግሊዝኛ ፊደላት ሲጻፍ 6+13+6) ነው:: ሰይጣን በኮሙኒዝም ሥርዓት የእግዚአብሔርን እምነት ለማጥፋት የሞከረበት መሣሪያ ኢ-አማኒነት ነው::

ሌላኛው ደም የጠማው ግለሰብ 6 ሚሊዮን አይሁዳውያንን የፈጀው አዶልፍ ሂትለር ነው:: በሂትለር የሥልጣን ዘመን ሕዝቡ



Scanned with CamScanner

እንዲያመልክ የተፈለገው ፉህረርን («መሪውን») ነበር፤ ሂትለርም ቢሆን ዓለምን የመግዛት ሕልም ነበረው:: ሂትለር የቀሰቀሰው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ ሂትለርና ውሽማው ራሳቸውን በመግደል ምሳቸውን ለማግኘት ተገድደዋል:: (በጦርነቱ 50 ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወቱን እንዳጣ ይገመታል::)

ናምሩድ፣ ናቡከደነፆር፣ ሃማን፣ ታላቁ እስክንድር፣ ጁሊየስ ቄሳር፣ ስታሊንና ሂትለር የመጪው የጥፋት ልጅ ተምሳሌቶች ወይም አመላካቾች ናቸው:: ፈርኦን፣ ቄሳር፣ ፉህረር፣ አምባገነን፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ወይም አውሬው ብለን ልንጠራው ብንችልም፣ የጥፋት ልጅ እነኝህን ሁሉ አጣምሮ የያዘ ነው:: ኃይል 13 «ዓለም አቀፍ ሰይጣናዊ ሥርዓት» ለመመሥረት የሚያደርገውን የመጨረሻ ሙከራውን ለማሳካት ቆርጦ የሚነሣ በመሆኑ የጥፋት ልጅ ሰይጣን ማሰባሰብ የቻለውን ጋኔናዊ ኃይል ሁሉ እንደያዘ ከዓለም ዙፋን ላይ ይቀመጣል::

«በመንግሥታቸውም መጨረሻ፣ ኃጢአታቸው በተሞላች ጊዜ፣ እንቅስቃሴን የሚያስተውል ፊቱ ጨካኝ ንጉሥ ይነሣል:: ኃይሉም ይበረታል፣ ነገር ግን በራሱ ኃይል አይደለም፤ በድንቅም ያጠፋል፤ ያደርግማል፣ ይከናወንማል፤ ኃያላንንና የቅዱሳን ሕዝብ ያጠፋል:: በመታለሉ ተንኰልን በእጁ ያከናውናል፤ ልቡም ይታበያል፤ ታምነውም የሚኖሩትን ብዙዎችን ያጠፋል፤ በአለቆቹም አለቃ ላይ ይቋቋማል፤ ያለ እጅም ይሰበራል::» (ትንቢተ ዳንኤል 8:23-25)



Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ 9

# ምሥጢረ 666

«ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው።»

(የማቴዎስ ወንጌል 4:9)

መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናችን ፍጻሜውን ስለሚያገኝ በርካታ ምልክቶች ዓመታት ዕድሜ ስላስቆጠረ ሴራ ተናግሯል። እግዚአብሔር ይህን በሚመለከት፣ ማለትም ስለ ምሥጢረ 666፣ ምን እንዳለ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን ከፍተን ሁለተኛይቱን የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ምዕራፍ 2 ቁጥር 1-12 ማንበብ ይኖርብናል።

«ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፣ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፣ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ መልእክት የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፣ ከአእምሯችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እለምናችኋለሁ። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፣ አይደርስምና። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፣ አምላክ ከተባለው ሁሉ ሰዎችም የሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው። ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፣ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁምን? በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፣ የሚከለክለውን ሁሉ ታውቃላችሁ። የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፣ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፣ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን



Scanned with CamScanner

ምሥጢረ 666 ከማክተሚያው የሚደርሰውም በእነኝህ ሰባት ዓመታት ነው።

የተሰሎንቄ ሰዎች የክርስቶስን መምጣት፣ ሕዝቡን የሚሰበስብና ትልቅ ጥፋት የሚወርድ መሆኑን የሚገልጹትን መሠረታዊ ትንቢቶች ዐውቀዋል። ይሁንና፣ በዘመናችን በርካቶች ግራ እንደተጋቡ ሁሉ፣ የትኛው ትንቢት እንደሚቀድም ተደናግረዋል።

አንዳንድ አማኞች ጥፋት የሚወርድበት ጊዜ ጀምሯል በማለት መንፈሳቸው እጅግ ተረብሿል። በእርግጥ፣ እንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ በማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ ፍርሃትን የሚያሳድር ነው። ይሁንና፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ» ይለናል። (ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2 5:9)

የክርስቶስ ሕዝቡን መሰብሰብ ከክርስቶስ መምጣት የተለየ ነው። ክርስቶስ ከሰማይ ወደ ሕዝቡ ይወርዳል። ሁሉም ሰው እንዲያየው፣ ኃይሉንና ጸጋውን በምድር ለማሳየት ይመጣል። ሕዝቡን የሚሰበስበው ለሰባት ዓመታት ከሚቆየው መከራና ችግር ከሚነግሥበት የጥፋት ጊዜ ቀደም ብሎ ነው። የጌታ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ቁጣ ይድናል። ሰባቱ የጥፋት ዓመታት እንዳበቁ የኃጢአት ሰው (ሰው 666) በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይጠፋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ «የዓመፅ ምሥጢር» («የክፋት ምሥጢር»፣ «የኃጢአት ምሥጢር»፣ አሊያም «ምሥጢረ 666») በሥራ ላይ እንደሆነ ተናግሯል። ባለፈው ምዕራፍ እንደተገለጸውም ለ6000 ዓመታት በሥራ ላይ ነው። ሴራው ከማክተሚያው ቢያንስ የሚደርሰው ለሰባት ዓመታት በሚቆየው የጥፋት ጊዜ ሲሆን፣ ከሰው 666 (የኃጢአት ሰው፣ የዓመፅ ሰው፣ የጥፋት ልጅ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ወይም አውሬው) ጋርም የተያያዘ ነው።

የመከራና የችግር ጊዜው ሲጀምር ይኸው እኩይ ሰው ይገለጣል ወይም ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት ግን ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚለው፣ እሱንና ሴራውን የገታቸው ነገር አለ። ታዲያ፣ ይህን እኩይ መርሃ ግብር የገታው ማን ነው? የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንት



Scanned with CamScanner

ለመጀመሪያ ጊዜ ለማየት በጉጉት እየጠበቁ ነው፤ እሱም ወደ ምድረ-በዳው ወርዶ ይቀበላቸዋል:: በዚህን ጊዜ «ሎሌው» በገነት ስለምትጠብቀን «ሙሽራ» ይነግረናል::

2. መንፈስ ቅዱስ የዓመፅ ምሥጢርን የሚከለክለውን እጅ ያነሣል:: እኩይነት በየቦታው ተሰራጭቶ ምሥጢረ 666 በሚገርም ፍጥነት በመላው ዓለም ላይ የዘረጋውን የቁጥጥር መረብ የሚያጠናክረው ይህን ጊዜ ነው::

3. የዓመፅ ሰው በምድር ላይ ይገለጻል:: እስከዚህን ጊዜ ድረስ እሱ ልክ እንደ አዳም ዌይስሆፕት በጥንቃቄ ተደብቆ ይቆያል:: የሴራው ማእከል እሱ ሲሆን፣ ማንነቱን የሚውቁትም በዙሪያው ያሉ ጥቂት ውስጠ-ዐወቆች ብቻ ናቸው::

## ክፋት

ክፋት ስንል በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም እያየነው ያለውን ማለታችን ብቻ ሳይሆን ከእውነት፣ ከእግዚአብሔር ቃል፣ እንዲሁም ከክርስቶስ ፍቅር በመራቅ የሚፈጠረውን ጭምር ነው:: ሐዋሪያው ጳውሎስ የተናገረው ከኃጢአት ሰው ጋር ስለተያያዘው ክፋት ነው:: ይህም ክፋት የእውነተኛው እምነት ውድቀትና የጨለማ ሃይማኖት እድገት ነው::

በሌላ ትንቢት ሐዋርያው ጳውሎስ፣ «መንፈስ ግን በግልጥ፡- በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል» ብሏል (ወደ ጢሞቲዎስ 1 4:1)::

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 7 ደግሞ ትንቢቱ በተለይ ምሥጢረ-ባቢሎን ስለተባለው የክፋት ሃይማኖታዊ ሥርዓት (ታላቋ ጋለሞታ) ይነግረናል:: «በግምባርዋም ምሥጢር የሆነ ስም፡- ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት ተብሎ ተጻፈ::» (የዮሐንስ ራእይ 16:5)

ይህ ሥርዓት «በጻድቃን ደምና በክርስቶስ ምስክሮች ደም ከሰከረ» በኋላ ራሱ በኃጢአት ሰውና በግዛቱ 10 «ነገሥታት» እጅ ይጠፋል:: «ያየሃቸውም አሥር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል፤ ሥጋዋንም ይበላሉ፣ በእሳትም ያቃጥሉአታል:: እግዚአብሔር አሳቡን እንዲያደርጉ አንድንም አሳብ



Scanned with CamScanner

በዚህ ምዕራፍ ስለ ሰይጣናዊው ሥላሴ እናነባለን:: እግዚአብሔር በአብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደሚገለጽ ሁሉ፤ ሰይጣንም በራሱ፣ በዓመፅ ሰውና፣ በሐሳዊው ነቢይ ይገለጻል:: በአምላኮተ-ሰይጣን ሃይማኖት ሰይጣን እግዚአብሔርን፣ የዓመፅ ሰው ወልድን፣ ሐሳዊው ነቢይ መንፈስ ቅዱስን እንደሚወክሉ ሆነው ይቀርባሉ::

በዚህ ምዕራፍ እነኝህ ሦስት እኩይ አካላት ዘንዶው፣ አውሬውና ሁለተኛው አውሬ በሚል ይገለጻሉ:: መጠሪያቸው በምዕራፉ ውስጥ 18 ጊዜ (6+6+6) ጊዜ ይጠቀሳል::

«አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፣ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ:: ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፣ እግሮቹ እንደ ድብ እግሮች፣ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ:: ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው:: ከራሶቹም ለሞት እንደ ታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፣ ለሞቱ የሆነውም ቁስል ተፈወሰ:: ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ፣ ለዘንዶውም ሰገዱለት፣ ለአውሬውም ሥልጣንን ስጥቶታልና፤ ለአውሬውም:- አውሬው ማን ይመስለዋል፣ እርሱንም ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት::

«ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፣ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው:: እግዚአብሔንርም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ:: ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፣ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው:: ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል::» (የዮሐንስ ራእይ 13:1-8)

የአውሬው ዐሥር ቀንዶች የሚወክሉት ከሮማውያን ግዛተ-አፄ የተፈጠሩትን ግዛቶች የሚገዙትን ዐሥር ነገሥታት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የናቡከደነፆርን ምስል ዐሥር የእግር ጣቶች ይወክላል:: የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ዳግም ያንሰራራውን የሮማውያን ግዛተ አፄ ትንቢት በዘመናችን እውን እያደረገ ለመሆኑ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ነው::



Scanned with CamScanner

የዚህ ዓይነቱ ሥርዓት አደጋ የዓለማችን ሕዝብ የጥቂቶችን ፍላጎት እንዲያሟላ የሚስገድድ መሣሪያ መሆኑ ነው፡፡ የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚጠቀምበት ሥርዓት ዓለማችን ሰይጣንን እንድታመልክ ለማስገደድ ያስችለዋል፡፡ ቁጥሩ በግምባራቸው ወይም በቀኝ እጃቸው ላይ እንዲነቀስ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ይገደላሉ፡፡ ከሞት አደጋው የሚተርፉት የሦስት ዓመት ከመንፈቅን ጊዜውን ተደብቀው ማሳለፍ የቻሉ ጥቂቶች ይሆናሉ፡፡ ምልክቱን የተቀበሉት ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ስለሚወርድባቸው ንቅሳት የክፉ ቀን ማኅተም ይሆናል፡፡

«…ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፣ እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፣ በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሠቃያል፡፡ የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፣ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የስሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም፡፡» (የዮሐንስ ራእይ 14፡9-11)

በዘመናችን ያሉ በርካታ ዓለም አቀፋዊ ንቅናቄዎች እያመሩ ያሉት ወደዚሁ ሰይጣናዊ ሴራ ፍጻሜ ነው፡፡ የሰይጣንን ዓላማና ግብ ከተገነዘብን፣ ለአንድ ዓለም መንግሥት ምሥረታ የሚደረገው ግፊት ምን ያህል እየጠቀመው እንዳለ ለመረዳት አንቸገርም፡፡ የዓለም መንግሥት ምሥረታውም ቢሆን የሰይጣን ሴራ አንድ አካል ነው፡፡

የዓለም መንግሥት ምሥረታን እውን ለማድረግ ከሚሠሩት መካከል እኩይ ዓላማ ያላቸው ሁሉም አይደሉም፤ ምናልባትም ጥቂቶች ብቻ ይሆኑ ይሆናል፡፡ ከነኝህ መካከል አብዛኛዎቹ ለእኩይ ዓላማ ማስፈጸሚያነት ጥቅም ላይ የዋሉ መሣሪያዎች መሆናቸውን አያውቁትም፡፡

# ምዕራፍ 10
# ዓለም አቀፋዊ መረብ

«ሕዝባብ በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው፣ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ትቆጥሪዋለህ፡፡»

(ትንቢተ ኢሳይያስ 40፡15)

የምሥጢረ 666 እጆች የዓለም ሀገራትን ሁሉ ያስተሳሰሩና ምድሪቷን በእቅፋቸው ውስጥ ያስገቡ ናቸው፡፡ ሳይ ሳዩን ሲታይ፣ ዓለም አቀፋዊ መረብ የሰው ልጅን እንደ አንድ ቤተሰብ የሚያቀራርብ ነው፡፡

ሀገራት ሁሉ «በአንድ ዓለም አቀፋዊ መንደር» ውስጥ እስከታቀፉ ድረስ እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ የጋራ ችግሮች ስላሉን በአንድ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ውስጥ የጋራ ትብብርና መፍትሔዎች ሊኖሩን ይገባል፡፡ «የጋራ መጻኢ ሕይወታችንን ለመጋራት እንድንችል በኅብረት መሰለፍ ይኖርብናል፡፡»

## የተባበሩት መንግሥታት

የአንድ ዓለም መንግሥት ምሥረታ እንዲህ በቀላሉ የሚሳካ ነገር አይደለም ብለው የሚያስቡ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ የመንግሥታቱ ማኅበር ጊዜውን ጠብቆ የከሰመ ዓለም አቀፍ ድርጅት ነው፡፡ ምንም እንኳ አሁንም ድረስ እየሠራ ያለ ቢሆንም፣ የተባበሩት መንግሥታት ያስገኝልናል ብለን የጠበቅነውን ሰላም ለማስፈን ዐቅመ ቢስ ሆኗል፡ ለዚህ የሚሰጠን ምላሽ ደግሞ፣ «ችግሩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥርስ የሌለው አንበሳ መሆኑ ነው፡፡ የዚህን ዓለም አቀፋዊ አካል ሥልጣን ካጠናከርነው ዓለም አቀፋዊ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ውጤታማ ይሆናል» የሚል ነው፡፡

ይህን ብናደርግ የተባበሩት መንግሥታት በጎ ዓላማ ባላቸውና እምነት በሚጣልባቸው ሰዎች የሚመራ ድርጅት እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተባበሩት መንግሥታት የተመሠረተው በቅን ልቦና ነው? ብለን መጠየቅ ሊኖርብን ነው፡፡ ከተባበሩት



Scanned with CamScanner

መንግሥታት ምሥረታ በስተጀርባ ካሉት አካላት መካከል አንዱ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት መሆኑን ልብ ልንል ይገባል::

ይህን መሥሪያ ቤት ከ1920ዎቹ ዓመታት ወዲህ የሚያሽከረክረው የውጭ ግንኙነት ካውንስል ነው:: ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲቀሰቀስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጦርነቱ ካበቃ በኋላ አዲስ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት የሚመሠረትበትን እቅድ የመንደፍ ኃላፊነት የተሰጠው አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ ነበር:: ይኸው የድኅረ-ጦርነት ችግሮች ኮሚቴ የኋላ ኋላ በድኅረ-ጦርነት የውጭ ፖሊሲ አማካሪ ኮሚቴ በሚል መጠሪያ እንዲዋቀር ተደርጓል:: የዚህ ኮሚቴ አባላት በሙሉ የውጭ ግንኙነት ካውንስል አባላት ነበሩ::

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ አልጀር ሂስ የተባለ የካውንስሉ አባል የልዩ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ቢሮ ዳይሬክተር ሆኖ ተሾመ:: ሂስ የውጭ ግንኙነት ካውንስል አባል ብቻ ሳይሆን የኮሙኒዝም ርዕዮተ-ዓለም አቀንቃኝ ጭምር ነበር::

ለአንድ ዓለም መንግሥት ምሥረታ የመጀመሪያው እርምጃ የሆነው የተባበሩት መንግሥታት እንዲቋቋም ትልቁን ሥራ የሠሩት የድኅረ-ጦርነት የውጭ ፖሊሲ ኮሚቴ፣ አልጀር ሂስና ሶቪዬቶች ናቸው:: የዩ.ኤስ. አሜሪካ ኮሙኒስት ፓርቲ አባላትም ለተባበሩት መንግሥታት ምሥረታ መጠነ-ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍና ጉጉት እንዲፈጥሩ ታዝዘዋል::

የተባበሩት መንግሥታት በተመሠረተበት በ1945 ዓ.ም. የሳን ፍራንሲስኮ ጉባኤ ላይ የድርጅቱ ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊ አልጀር ሂስ ነበር:: የአሜሪካ ልኡካን ቡድንን የወከሉት ኔልሰን ሮክፌለርን ጨምሮ 74 የውጭ ግንኙነት ካውንስል አባላት ነበሩ::

በ18 ኤክር (6+6+6) ላይ ለተገነባውና በኒው ዮርክ፣ ማንሃታን የሚገኘው የተባበሩት መንግሥታት ሕንጻ መሬቱን የለገሰው ኔልሰን ሮክፌለርና ቤተሰቡ ነው:: ሕንጻው በመንገዶች መካከል ያሉ ስድስት ብሎኮችን፣ ማለትም ከ42ኛ እስከ 48ኛ ጐዳና (6x7፣ 6x8)፣ የሚሸፍን ነው:: 39 ፎቆች (13x3) ያሉት ይህ ሕንጻ ግንባታው የተካሄደው

ለአንዳንዱ የዓለማችን ችግሮች «መፍትሔ» ለመስጠት ያቀዱ ተጨማሪ ዓለም አቀፍ መሥሪያ ቤቶችን ለማቋቋም ጥቅም ላይ ይውላል:: ይህም አካሄድ ሀገራት ይበልጥ በዓለም አቀፋዊው ተቋም ላይ እምነታቸውን እንዲጥሉ ያደርጋቸዋል:: እነኝህ ሀገራት የኋላ ኋላ በችግሮችና በፕሮፓጋንዳ አማካኝነት ሉዓላዊነታቸውን ለአንድ ዓለም መንግሥት እንዲያስረክቡ እየተመቻቹ እንደሆነ የሚገነዘቡ ጥቂቶች ናቸው::

## የተባበሩት የዓለም ፌደራሊስቶች

የተባበሩት የዓለም ፌደራሊስቶች ኖርማን ካዚንስና ጀምስ ፐ. ዋህበርግ የተባሉ ሁለት የውጭ ግንኙነት ካውንስል አባላት በ1947 ዓ.ም. ያቋቋሙት ድርጅት ነው:: ለዩ.ኤስ. አሜሪካ ሴኔት የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ፣ «ወደድንም ጠላንም፣ በኃይልም ሆነ በውዴታ የዓለም መንግሥት ይኖረናል» ሲል የተናገረው ጀምስ ዋርበርግ ነው::

ድርጅቱ ከካውንስሉ ጋር የተቆራኘ ከመሆኑም ሌላ፣ የዚሁ ምሥጢራዊ ማኅበር ሽፋን ነው:: የተባበሩት የዓለም ፌደራሊስቶች ዓላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ የድርጅቱ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ሎርድ ሜየር ጁኒየር ሀገራት በተባበሩት መንግሥታት ቁጥጥር ሥር አንድ ፌደሬሽን የመመሥረታቸውን አስፈላጊነት የጻፈበትን ፒስ ኦር አናርኪ መጽሐፍ ማንበቡ በቂ ነው:: መጽሐፉ እንደሚለው፣ «አንድ ሀገር ከአንድ ዓለም ፌደራል መንግሥት ጋር ከተቀላቀለ በኋላ መነጠልም ሆነ ማመፅ አይችልም... ምክንያቱም አቶሚክ ቦምብ የታጠቀ (የዓለም) ፌደራል መንግሥት ይህን የሞከረውን ሀገር ከምድረ-ገጽ ያጠፋዋልና::»

## ቢልደርበርገሮች

በእንግሊዝኛ ሲጻፍ 13 ፊደላትን የያዘው ይህ ተቋም ከዓለማችን ስመ-ጥር ድርጅቶች መካከል አንዱ ነው:: በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ከሕዝብ ተገልለው በምሥጢር የሚሰበሰቡ ፖለቲከኞችን፣ ባንከኞችንና ባለሀብቶችን የመሰሉ የዓለማችንን ኀያላን ያቀፈ አካል ነው::

ለዚሁ ዓለም አቀፋዊ የውስጠ-ዐወቆች ቡድን ምሥረታ ትልቁን ሚና ከተጫወቱት ሰዎች መካከል አንዱ የኔዘርላንዱ ልዑል በርንሃርድ

ነው:: ልዑል በርንሃርድ የቀድሞዋ ንግሥት ጁሊያና ባለቤት ነው:: ድርጅቱ የተመሠረተው በ1956 ዓ.ም. ሲሆን፣ መጠሪያ ስሙንም ያገኘው የመጀመሪያ ጉባኤውን ካካሄደበት የሆላንዱ ቢልደርበርግ ሆቴል ነው::

ልዑል በንሃንርድ በ1976 ዓ.ም. ከሎክሂድ ቅሌት ጋር በተያያዘ ከ$1 ሚሊዮን የበለጠ ጉቦ ተቀብሏል በሚል ክስ ይመሠርትበታል:: ይህንንም ተከትሎ አብዛኞቹን የመንግሥት ሥልጣኖቹን እንዲለቅ ጫና ያርፍበታል:: ከዚህ በተጨማሪም፣ በ1977 ዓ.ም. የቢልደርበርገሮች ሊቀመንበርነቱንም ለመልቀቅ ተገድዷል:: ቀጣዩ የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆኖ የተመረጠው ሎርድ ሆም ነው::

ከታዋቂ ቢልደርበርገሮች መካከል ባሮን ኤድመንድ ደ ሮትሺልድ፣ የቀድሞው የምዕራብ ጀርመን ቻንስለር ሄልሙት ሽሚድት፣ የቀድሞው የፊያት ኩባንያ ፕሬዚዳንት ጆቫኒ አኜሊ፣ የቀድሞው የአይስላንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ጌይር ሃልግሪምሰን፣ የቀድሞው የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር ቶርብዮርን ፋልዲን፣ የቀድሞው የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ሮበርት ማክናማራ፣ የቀድሞው የዓለም ገንዘብ ድርጅት ኃላፊው ፒየር ፖል ሽዌይትዘር፣ ዴቪድ ሮክፌለር፣ የሌህማን ብራዘርሱ ጆርጅ ቦል፣ የዲለን፣ ሪድና ኩባንያው ሲ. ዳግላስ ዲለን፣ እንዲሁም ዶክተር ሄንሪ ኪሲንጀር ተጠቃሾች ናቸው:: ሌሎች የአውሮጳ መሪዎችም እንዲሁ የድርጅቱ አባላት ናቸው::

ድርጅቱ አማካሪ ኮሚቴ የተባለ አንድ አካል አለው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ 39 ውስጠ-ዐወቆችን ያቀፈ አመራር ሰጪና አስተባባሪ ኮሚቴ አለው:: (የዚህ ኮሚቴ አባላት ብዛት 40 ሳይሆን 39 [13+13+13] እንዲሆን የተፈለገው ለምንድን ነው? ቡድኑ ጠቅላላ ጉባኤም አለው::

ቢልደርበርገር ከውጭ ግንኙነት ካውንስል ጋር የተጠላለፈ ነው:: የቢልደርበርገር አመራር ሰጪና አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በሙሉ የካውንስሉ አባላት ናቸው:: ቢያንስ ሦስት ቀደምት የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ቢልደርበርገሮች ነበሩ:: በፈረንሳይ የሚገኘው የሮትሺልድ ቤተሰብ ከንግድ ጋር በተያያዘ ከልዑል በርንሃርድ ጋር



Scanned with CamScanner

የሌለው ዶክተር ፔቼይ በወቅቱ የፊያት ኩባንያ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ ነበር::

ክበቡ በ1973 ዓ.ም. ቢያንስ ከ26 ሀገራት የመጡ 100 ያህል ሰዎችን በአባልነት ያቀፈ ነበር:: ክበቡ ዳግም ያንሰራራል ከተባለው የሮማውያን ግዛተ-አፄና የምሥጢረ 666 ዓላማን ከሚያሳካው ዓለም አቀፋዊ ሴራ ጋር የተያያዘ ነው:: አዲስ የዓለም ሥርዓት እውን እንዲሆን ፍላጎቱ እንዳለው ለመረዳት ዶክተር ፔቼይ፣ «ከነኝህ ውሳኔዎች ላይ መድረስ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ ዓለም አቀፋዊ አካሄድ በመከተል ነው:: በኢኮኖሚው ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊና ፖለቲካዊ መስኮችም አዲስ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት መመሥረት አለበት» ማለታቸውን ማወቁ በቂ ነው::

የሮም ክበብ ከውስጠ-ዐወቆቹ ጋር ግንኙነት እንዳለው እንደንጠራጠር የሚያደርገን ጣልያን ውስጥ በሚገኘው የሮክፌለር ቤተሰብ ርስት ውስጥ በሚያዝያ 1968 ዓ.ም. (328x6) መመሥረቱ ነው:: የሮም ክበብ በጡረታ የተገለሉ ሰዎች ለውይይት ወይም ለመዝናናት የሚሰበሰቡበት አይደለም:: ከክበቡ ዐላማዎች መካከል አንዱ በሮም ክበብ በተሾሙ ኮሚሳሮች የሚመሩ ዐሥር የዓለማችንን ክልሎች ማዋቀር ነው:: የሮም ክበብ ኃይል 13 አዲስ የዓለም ሥርዓት ለመመሥረት የወጠነውን እቅድ ለመተግበር ከሚራወጡት ተሰሚነት ካላቸው በርካታ ድርጅቶች መካከል አንዱ ነው::



Scanned with CamScanner